በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# የእምነት ሕይወት - መግቢያ!!

መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com

*ቦታ፡-* ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

**የካቲት ፳ ቀን ፳፻፫ ዓ.ም.**

# <u>የእምነት ሕይወት - መግቢያ</u>

- እምነት የሕይወት መንገድና ወደ ሕይወት የሚመራንንም መደገፍ እንጂ በጸሎተ ሃይማኖት የምንመሰክረውን የሃይማኖት አቋም መቀበል ብቻ አይደለም፡፡
- እግዚአብሔርን ካልወደድነው፣ ካልታዘዝነው ብሎም ከእርሱ ጋር ኅብረት ካላደረግን እናምናለን ማለታችን ወይም ወደርሱ የምናቀርበው ልመናችን ብቻ ምን ረብ/ጥቅም አለው?
- ስለ ዘላለማዊ ሕይወት ወይም ከሞት በኋላ ስለሚጠብቀን ደስታስ መናፈቅ በንስሐና በመንፈሳዊ ሕይወት ሳንኖር ምን ይረባናል?
- በመንፈሳዊ ፍሬያትስ ሳንበለጽግ በመንፈስ ፍሬዎች ማመናችንስ ስለምን ይጠቅመናል?
- ነፍስን ማዳን በማይችል ተግባራዊነት በጎደለው እምነት በመኖርና በሕይወታችን ፍሬያቱ በተግባር በሚታዩ እምነት መካከል ከፍተኛ ልዩነት አለ፡፡
- ይህ ትምህርት የተዘጋጀው ቅዱስ ጳውሎስ ***<u>ካል ቆሮ 13፡5</u>*** ‹‹በሃይማኖት ብትኖሩ ራሳችሁን መርምሩ፡፡›› እንዳለው የእምነትን ትርጉም፣ ደረጃዎቹንና ዓይነቶቹን ብሎም በሕይወታችን ስላለው ታላቅነትና ጥቅም ለማስረዳት ሲባል ነው፡፡
- የምንመዘነው ***<u>ማቴ 7፡16</u>*** ‹‹በፍሬያቸው ታውቁአቸዋላችሁ፡፡›› እንዳለው በፍሬያችን እንጂ እምነት አለኝ ስላለን ብቻ አይደለም፡፡
- የሚያምን ሰው ልቦናም ሆነ ሕይወት ሳይገኝባቸው እናምናለን የሚሉ ሰዎች ይገጥሙናል፡፡ ታዲያ የሚያምን ሰው ሕይወት እንዴት ያለ ነው?

# የእምነት ሕይወት - መግቢያ

- የእምነት ሕይወት ከሰላማዊነት፣ ከጸጥተኛነትና ካለመጠራጠር ጋር የተቆራኘ ነው፡፡ ፈርተን ብንገኝ እንኳ ጌታችን *ማቴ 14፡31* ‹‹አንተ እምነት የጎደለህ፥ ስለምን ተጠራጠርህ? ›› በማለት ሲወቅሰን ይገኛል እንጂ ፍርሃታችን ተቀባይነት አያገኝም፡፡
- የሚያምን ሰው በሕይወቱ እግዚአብሔር የምሠራውን ያያል፣ ይሰማል፣ ይጽፈዋልም እያለ ስለሚሰማው የእግዚአብሔር መኖር የሚነበብበት ሥነ ምግባሩም የተቃና ነው፤ የሚያስነውርንም ነገር ወይም ጥፋትን በእግዚአብሔር ፊት ከመሥራት ይቆጠባል፤ ለማሰብም እንኳ ይፈራል፡፡
- እግዚአብሔርን የሚያምን ሰው ሕይወት ራሱን ለእግዚአብሔር ተገዢ በማድረጉ ይታወቃል፡፡
- እግዚአብሔርን የምናምን ከሆን በሕይወታችን የሚሆነው ሁሉ በእግዚአብሔር ፈቃድ የሆነና ለጥቅማችን - ለበጎ የተደረገ አድርገን አምነን እንቀበላለን፡፡
- በዚህም አቅጣጫችን የእግዚአብሔር ልጆች የሆን ሁሉ እግዚአብሔር በሰጠን ነገር በሰላም በእርካታና በደስታ እንኖራለን፡፡
- በእምነት ሕይወት ውስጥ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር አለ ማለት አይታወቅም፡፡ *ማር 9፡23፡፡* ‹‹ለሚያምን ሁሉ ይቻላልና››
- ስለዚህ የሚያምን ሰው በጨነቀው ጊዜ እግዚአብሔር በርካታ መፍትሔዎች አሉት፣ እንደፈቃዱም ያደርግልኛል፣ ነገሮችንም ያስተካክልልኝ ዘንድ ጣልቃ ይገባል… ብሎ ያምናል እንጂ አይታወክም አይናወጥም፡፡

# <u>የእምነት ሕይወት - መግቢያ</u>

- የሚያምን ሰው እግዚአብሔር በጥበቡ የሚሠራውንና በፍቅሩ ያደረገውን ሁሉ አምኖ ይቀበላል እንጂ እግዚአብሔርን ስለ ሥራው አይከራከረውም፡፡
- የሚያምን ሰው ከሚታየው ይልቅ በማይታየው ነገር ላይ ታላቅ ትኩረት ያደርጋል፡፡ ***<u>2ኛ ቆሮ 4፡18፡፡</u>*** ‹‹የማይታየውን እንጂ የሚታየውን ባንመለከት፥ ቀላል የሆነ የጊዜው መከራችን የክብርን የዘላለም ብዛት ከሁሉ መጠን ይልቅ ያደርግልናልና፤ የሚታየው የጊዜው ነውና፥ የማይታየው ግን የዘላለም ነውና።››
- የእምነት አርበኞች የምንላቸው በፍቅር ኖረው ፍሬያማ ሕይወትን የመሩ ጭምር እንጂ ስለ እምነታቸው ምስክር ሆነው የሞቱ ብቻ አይደሉም፡፡
- ስለዚህ በተመረጠው ርዕስ ሥር የምንማረው የእምነትን ሕይወት እንዴት እንደምንጎናጸፍ በርግጥም በእምነት አለመሆናችንን እንዴት እንደምንገመግም የሚያስረዳንን ትምህርት ነው፡፡
- እግዚአብሔርን ደስ ስለማሰኘት በተነገረበት ክፍልም የእምነት አስፈላጊነት ***<u>ዕብ 11፡6</u>*** ‹‹ያለ እምነትም ደስ ማሰኘት አይቻልም፤ ወደ እግዚአብሔር የሚደርስ እግዚአብሔር እንዳለ ለሚፈልጉትም ዋጋ እንዲሰጥ ያምን ዘንድ ያስፈልገዋልና።›› በማለት ተገልጧል፡፡
- እምነት ጸንተው ከሚኖሩ ከሦስቱ አንዱ እንደሆነ ***<u>1ኛ ቆሮ 13፡13</u>*** ‹‹እምነት ተስፋ ፍቅር እነዚህ ሦስቱ ጸንተው ይኖራሉ›› እንዲሁም ስለጻድቅ ሕይወትም ***<u>ዕብ 10፡38፡፡</u>*** ‹‹ጻድቅ ግን በእምነት ይኖራል፡፡›› በማለት ተጽፎልናል፡፡

# የእምነት ሕይወት - መግቢያ

- እምነት ወደ እግዚአብሔር የምንደርስበት የመጀመሪያ መንገድ ነው፡፡
- እንግዲህ በእግዚአብሔር ቅዱሳት መጻሕፍት፣ በመላእክቱ፣ በቅዱሳኑ ሁሉ ካላመንን እርሱ በእኛ እኛም በርሱ እንዴት ልንኖር ይቻለናል? ትእዛዛቱንስ እንዴት መጠበቅ ይሆንልናል? ለመዳናችን ዋናውና የመጀመሪያው አስፈላጊ ነገር እምነት ሲሆን እርሱም ወደ እግዚአብሔር የሚያደርሰን ነው፡፡ ***ማር 16፡16*** ‹‹ያመነ የተጠመቀ ይድናል፡፡››፣ ***ዮሐ 3፡16*** ‹‹በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።››፣ ***ዮሐ 3፡18*** ‹‹በእርሱ በሚያምን አይፈረድበትም፤ በማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ስላላመነ አሁን ተፈርዶበታል።››፡፡
- ጌታችንም አይሁድን ***ዮሐ 8፡24፡፡*** ‹‹እኔ እንደሆንሁ ባታምኑ በኃጢአታችሁ ትሞታላችሁና።›› ብሎአቸዋል፡፡
- ድኅነት በጌታችን ደም በኩል የተደረገልን ቢሆንም ቅዱስ ጳውሎስና ሲላስ ለእርስ ቤት ጠባቂው ***የሐዋ 16፡31*** ‹‹በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ አሉት።›› እንደተናገሩት ለመዳናችን መፈጸም እምነት ያስፈልገናል፡፡
- በዚህ እውነት ላይ የተመሠረተው የእምነት ወንጌል ለዓለም ተሰብኳል ተጽፎልናልም፡፡
- ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ ***ዮሐ 20፡31*** ‹‹ነገር ግን ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ ታምኑ ዘንድ፥ አምናችሁም በስሙ ሕይወት ይሆንላችሁ ዘንድ ይህ ተጽፎአል።›› በማለት የጻፈልንም ይህንኑ ለማስረዳት ነው፡፡

# የእምነት ሕይወት - መግቢያ

- **እምነት ከእግዚአብሔር ጋር የምንመሠርተው የመጀመሪያና ዘመናችንን ሁሉ ከእርሱ ጋር የምንመራው ሕይወት ከመሆኑ ባሻገር በጽድቅ ላለም ሕይወት የሚጠቅም ነው።** ***ዕብ 11፡7*** ‹‹ኖኅ ገና ስለማይታየው ነገር ተረድቶ እግዚአብሔርን እየፈራ ቤተ ሰዎቹን ለማዳን መርከብን በእምነት አዘጋጀ፥ በዚህም ዓለምን ኰነነ፥ በእምነትም የሚገኘውን ጽድቅ ወራሽ ሆነ።››፣ ***ያዕ 2፡23፡፡*** ‹‹አብርሃምም እግዚአብሔርን አመነ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት ያለው ተፈጸመ፤ የእግዚአብሔርም ወዳጅ ተባለ።››
- **መጽሐፍ ቅዱስ እንደ እምነታችን እንደሚፈረድልን ወይም እንደሚፈረድብን ሲመክረን** ***ሮሜ 5፡1*** ‹‹እንግዲህ በእምነት ከጸደቅን በእግዚአብሔር ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምን እንያዝ፡፡›› **ይለናል፡፡**
- **እምነት የሚደረጉልንንም ሆነ የተደረጉልንን ተአምራት ለመቀበል አስፈላጊያችን ነው፡፡ ጌታችን በኢያሪኮ ለተገናኘው ዓይነ ስውር** ***ሉቃ 18፡42*** ‹‹ኢየሱስም፡- እይ፤ እምነትህ አድኖሃል አለው።››፣ ***ማር 10፡52*** ‹‹ኢየሱስም፡- ሂድ፤ እምነትህ አድኖሃል አለው። ወዲያውም አየ በመንገድም ተከተለው።›› **የተናገረው ምን ያህል ድንቅ ነው?**
- **በለምጽ ለተያዘውም ሰው** ***ሉቃ 17፡19*** ‹‹እርሱንም። ተነሣና ሂድ፤ እምነትህ አድኖሃል አለው።››፣ **ለዕውራኑም** ***ማቴ 9፡29*** ‹‹በዚያን ጊዜ። እንደ እምነታችሁ ይሁንላችሁ ብሎ ዓይኖቻቸውን ዳሰሰ።›› **ተብሎ የተጻፈልንም የሚያስረዳን የእምነትን አስፈላጊነት ነው፡፡**
- **በሌላ በኩል ባደገበት በናዝሬት ባለማመናቸው የተነሳ** ***ማቴ 13፡58*** ‹‹በአለማመናቸውም ምክንያት በዚያ ብዙ ተአምራት አላደረገም።›› **ተብሎ የእግዚአብሔር ኃይል ተአምራትን ሊያደርግልን ቢችልም ማመናችን አስፈላጊ እንደሆነና የሚደረግልንም እንደ እምነታችን እንደሆነ ተገልጦልናል፡፡**

# የእምነት ሕይወት - መግቢያ

- ዲዳ (የማይናገር) መንፈስ ያደረበት ልጅ አባት *በማር 9፡24* ‹‹ብዙ ጊዜም ሊያጠፋው ወደ እሳትም ወደ ውኃም ጣለው፤ ቢቻልህ ግን እዘንልን እርዳንም አለው። ኢየሱስም፦ ቢቻልህ ትላለህ፤ ለሚያምን ሁሉ ይቻላል አለው። ወዲያውም የብላቴናው አባት ጮኾ። አምናለሁ፤ አለማመኔን እርዳው አለ። ›› በእምነቱ ደካማ ስለነበር እግዚአብሔርም እንደ እምነታችን እንደሚያደርግልንና በሌላም በኩል እናምን ዘንድ ተአምራትን እንደሚሠራልን የተጻፈልንን እንረዳለን፡፡
- ከዚህም የምንረዳው እምነት ከተአምራት አስቀድሞ ወይም ተአምራቱ ስለማመናችን ሊደረግ እንደሚችል ነው፡፡
- እምነት የኃይል ምንጭ ነው፡፡ አንድ የሚያምንበት ሐሳብ ያፈለቀ ሰው በእግዚአብሔር ኃይል ይህን ሐሳቡን ሊፈጽም ሲጣጣር ሲፈጽመውም እንመለከታለን፡፡ እምነቱ ጥንካሬን ብርታትንና ድፍረትን ሰጥቶታልና፡ ባያምን ግን እነዚህ ሁሉ አይኖሩትም አይፈጸሙለትምም፡፡
- እምነት ባለበት ኃይል አለ፤ በእምነት የሚደረግም ጸሎት ኃያል ነው፡፡
- በጸሎትና ጸሎትም በሚሠራው የሚያምን ሰው በብርታት፣ በኃይልና በመታመን ይጸልያል፡፡
- በሚናገረው በእያንዳንድዋ ቃል የሚያምን ሰባኪ የሚሰብከው ስብከት ኃያል ነው፡፡ በቃሉም አማካይነት የሚያምነው እምነት በስብከቱ አማካይነት ወደ ሚሰሙት ሰዎች ልብ ይገባል፡፡
- እምነት አብረውት በሚገለጡ የእምነት ፍሬዎች የበለጠ ግልጥ ይሆናል፡፡ ፍሬዎቹም ሰላም፣ ጥንካሬ፣ ጸጥተኛነት፣ በትጋት መሥራት ናቸው፡፡ እነዚህም ፍሬዎች የቅድስና ሕይወት፣ ራስን ለእግዚአብሔር አሳልፎ የመስጠትና ለርሱም ምስክሮች የመሆን… ምልክቶች ይታዩበታል፡፡

# የእምነት ሕይወት - መግቢያ

- እምነት የመዳናችን፣ የፈውሳችን፣ የመንፈሳዊ ፍሬዎች ብሎም ***ማር 9፡23*** ‹‹ለሚያምን ሁሉ ይቻላል አለው።›› እንደተጻፈው የእግዚአብሔር የተአምራቱ መሠረት (ምንጭ) ነው፡፡
- አማኝ የሚለውን ስም ይዘው የማያምን ልብ ያላቸው ሰዎች ሊገጥሙን ይችላሉ፡፡
- እምነት መንፈሳዊ ሕይወትን የሚዳስስ በማመን የሚደረጉልንንም ተአምራት ስለሚያጠቃልል የእግዚአብሔርን ኀልዎት ከሚያምኑ ቤተሰቦች መወለዳችን ብቻ ብቁ አማኝ አያደርገንም፡፡
- በአንድ ወቅት ደቀመዛሙርቱ በአጋንንት የተያዘውን ሰው ስለምን ማዳን እንደተሳናቸው ጌታችንን በጠየቁበት ክፍል ***ማቴ 17፡17-20*** ‹‹ ኢየሱስም መልሶ፦ የማታምን ጠማማ ትውልድ ሆይ፥ እስከ መቼ ከእናንተ ጋር እኖራለሁ? እስከ መቼስ እታገሣችኋለሁ? ወደዚህ ወደ እኔ አምጡት አለ። ኢየሱስም ገሠጸው ጋኔኑም ከእርሱ ወጣ፥ ብላቴናውም ከዚያች ሰዓት ጀምሮ ተፈወሰ። ከዚህ በኋላ ደቀ መዛሙርቱ ብቻቸውን ወደ ኢየሱስ ቀረቡና። እኛ ልናወጣው ያልቻልን ስለ ምን ነው? አሉት። ኢየሱስም፦ ስለ እምነታችሁ ማነስ ነው፤ እውነት እላችኋለሁ፥ የሰናፍጭ ቅንጣት የሚያህል እምነት ቢኖራችሁ፥ ይህን ተራራ። ከዚህ ወደዚያ እለፍ ብትሉት ያልፋል፤ የሚሳናችሁም ነገር የለም።›› ብሎ መልሶላቸዋል፡፡
- ይህ የሰናፍጭ ቅንጣት የሚያህል እምነት ምንድር ነው? ***ካል ቆሮ 13፡5*** ‹‹ በሃይማኖት ብትኖሩ ራሳችሁን መርምሩ፤ ራሳችሁን ፈትኑ፤ ወይስ ምናልባት የማትበቁ ባትሆኑ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ በእናንተ ውስጥ እንዳለ ስለ እናንተ አታውቁምን?›› እንዳለን ራሳችንን እንመርምር፡፡
- ***በማቴ 7፡21-23*** እንደተጻፈልን … ጌታ ሆይ… ማለት ብቻውን የስም ወይም የሐሳብ እምነት እንጂ በእግዚአብሔር ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

# የእምነት ሕይወት - መግቢያ

- ሙሽራውን ዘይቱ ያለቀበት መብራት ይዘን ወይም ደጁ ከተዘጋ በኋላ እንደ ሰነፎቹ ደናግል መጠበቅ ወይም መድረስም አይጠቅመንም፡፡
- እምነት ማመን ብቻ ሳይሆን ሕይወትም ነው፡፡ ሕይወቱንም በውስጣችን ከሚኖረው ፍሬ እንቀምሳለን፡፡ ***ማቴ 7፡16-20***፡ ታዲያ እምነታችን ፍሬ አለው?
- ***ቀዳ ዮሐ 2፡3-4*** ‹‹ትእዛዛቱንም ብንጠብቅ በዚህ እንዳወቅነው እናውቃለን። አውቄዋለሁ የሚል ትእዛዛቱንም የማይጠብቅ ውሸተኛ ነው እውነትም በእርሱ ውስጥ የለም። ቃሉን ግን የሚጠብቅ ሁሉ በእርሱ የእግዚአብሔር ፍቅር በእውነት ተፈጽሞአል። በእርሱ እንዳለን በዚህ እናውቃለን፤›› እንደተባለ እምነት ለእግዚአብሔር ትእዛዝ በመታዘዛችን ይፈተናል ይረጋገጣልም፡፡ የማይታዘዝም እውነተኛ አማኒም ሆነ ክርስቲያን ሆኖ አይቆጠርም እግዚአብሔርንም አያውቅም፡፡
- እንደ ደቀመዛሙርቱ ጥልቅ የሆነ ሃይማኖታዊ ዕውቀት ባይኖረንም ካመንን አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ያደረገውን የሄኖክን መንፈሳዊ ሕይወት መምራት ግን እንችላለን፡፡ ሄኖክ ‹‹አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር በማድረግ … ደስ አሰኝቶታል፡፡›› ***ዕብ 11፡5-16፣ ዘፍጥ 5፡22-24፡፡***
- አባታችን አብርሃም የእምነት ሰው ነበር፡፡ ወዴት እንደሚሄድ ሳያውቅም እግዚአብሔር ሲጠራው ወጣ፡፡ አብርሃም የተከተለው የእግዚአብሔርን የጊዜ ሰሌዳ ነው፣ በመቀጠልም እግዚአብሔር ሙታንን እንደሚያስነሳ በማመን ልጁን መሥዋዕት አድርጎ አቅርቧል፡፡ ***ዕብ 11፡8-17-19፡፡***

# <u>የእምነት ሕይወት - መግቢያ</u>

- ሚስቱ ሣራም እግዚአብሔር የተናገረውን እንደሚፈጽም በማመንዋ የእምነት አርበኛ ናት፡፡ ***<u>ዕብ 11፡11</u>***
- በእግዚአብሔር ያመኑ፣ ከርሱ ጋር የተጓዙ፣ በጽድቅ የተራመዱ፣ ደስ ያሰኙትም የእምነት አርበኞች ናቸው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስም በዚህ መንገድ የእምነትን ትርጉም በስፋት አስረድቶናል፡፡ ***<u>ዕብ 11፡35-39</u>***
- ቅዱስ ጳውሎስ ***<u>ዕብ 11፡1</u>*** ‹‹እምነትም ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያስረግጥ፥ የማናየውንም ነገር የሚያስረዳ ነው።›› አስረድቶናል፡፡
- ከሞትን በኋላ በሕያው አካል ተነስተን እግዚአብሔርን እንደምንገናኝ፣ ከቅዱሳኑና ከመላእክቱ ጋርም ፍጹም የሆነውን ዝማሬ እንደምንዘምር ተስፋ እናደርጋለን፡፡ ይህም ሳናየው ስለተነገረን ብቻ ተስፋ የምናደርገው ነው፡፡
- እምነት እነዚህን ሁሉ ባናያቸውም እንኳ አሉ፣ ይሆናሉ፣ ይደረጋሉ ብሎ ያለጥርጥር በፍጹም ድፍረት ማመን ነው፡፡ በእምነታችን ያጽናን፡፡ አሜን፡፡

ይቆየን፡፡

For your queries or questions E-mail:

kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :

www.zeorthodox.org